## በከተማችን ከዚህ በፊት ይሠራበት የነበረው የምርጫ ቀን እንዲለወጥ ይፈልጋሉ?

## የከተማችን ምክር ቤት በምርጫ ቀን ለውጥ ጉዳይ ከከተማው ኗሪዎች ጋር ለመወያየት ይፈልጋል።

የከተማችን የምርጫ ቀን ከሜሪላንድ አጠቃላይ የክልል ምርጫ ቀን ጋር በአንድ ጊዜ እንዲሆን ለከተማችን ምክር ቤት በ **2015** ዓ/ም ድጋፋችሁን ሰጥታችሁ እንደነበር ይታወሳል።

ምክር ቤቱ የእናንተን ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ እና የምርጫ ቀኑም ከ **2018** ዓ/ም ጀምሮ እንዲተገበር ለማድረግ ሕገ ደምብ ለማሻሻል፦

1. ምክር ቤቱ የምርጫ ቀኑን ከኅዳሎ ወደ ሙሉ ዓመት መቀየር፤
2. በ **2017** ዓ/ም የተመረጡትን የከተማችንን ከንቲባና የምክር ቤት አባላት የምርጫ ዘመን በአንድ ዓመት ብቻ እንዲገደብና በሚመጣው ዓመት ኅዳር **2018** ዓ/ም በሚደረገው ምርጫ የምትመርጧቸው ግለሰቦች ከሜሪላንድ የክልል ተመራጮች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ተመርጠው የሁለት ዓመት የአገልግሎት ዘመን እንዲኖራቸው የሚደረገው ህግ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

በዚህ በሚሻሻለው ሕገ ደምብ መሠረት መራጮች ለ **2018** ዓ/ም ምርጫ ሲመጡ በመጀመሪያ ለክልል ምክር ቤት ተወዳዳሪዎችን መርጠው እንደጨረሱ የከተማችንን እጩዎች ደግሞ በተመሳሳይ ቦታ እና ቀን ነገር ግን ለከተማችን ምርጫ ማስፈጸሚያ በሚዘጋጀው በሚቀጥለው ክፍል ይመርጣሉ።

የከተማችን ምክር ቤት ይህንን የሕገ ደምብ ማሻሻያ ቅድመ ዝግጅት ከመጀመሩ በፊት ከከተማው ኗሪዎች ጋር ውይይት ስለሚያደርግ **መጋቢት 10 ቀን 2009 ዓ/ም ከምሽቱ 1:30** ላይ በከተማው ጽ/ቤት በሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ **(March 1, 2017 at 7:30pm, Takoma Park Community Center, 7500 Maple Ave.)** እንድትገኙ እያሳሰብን ጥያቄ ለመጠየቅ ወይንም አስተያየት ለመስጠት የምትፈልጉ ኗሪዎች ካላችሁ በኢ-ጦማር **clerk@takomaparkmd.gov** መልእክታችሁን መላክ እንደምትችሉ ከወዲሁ ለመጠቆም እንወዳለን።